# አሻሮ ነው ምሴ

ተዘንግቶ እንጂ ፤ መቼ አዲስ ሆነና
መጠየቅ ይቻላል ፤ የሚያውቁኝን አምና
ሲገነቡ ማፍረስ ፤ ነው የኔ ቀኖና
የተካንኩ ካህን ፤ ያውም በብተና
አልጋ ሲሉኝ መሬት ፤ እወዳለሁና
ለምን ደነቃችሁ ፤ ገንጣይ አቀፍኩና ?

ጮማ ቁርጥ አይቀምስም ፤ አይወድም ምላሴ
ጥሩ አይወድልኝም ፤ መች ታድላ ነፍሴ
ዛሬ አዲስ ሆነ ወይ ፤ የኔ መልከስከሴ
አሻሮ እያንጋፈፍኩ ፤ ሞልቼ በኪሴ
ተገዝቼ ብያዝ ፤ ባቦ በስላሴ
ወሊሶ ብጠመቅ ፤ ቢያዘንቡ ቅዳሴ
ተሰድጄ ብሄድ ፤ አውሮፓ ዩኤሴ
ጥሩ አይወድልኝም ፤ አሻሮ ነው ምሴ ።

አሻሮ ናት ምሴ ፤ ከጥንት ከጠዋቱ
አላማዬ ስንኩል ፤ አድርጎኛል ከንቱ
ሲጮሁ የሚያስጮኸኝ ፤ የገደል ማሚቱ
ለኔ ተስማምቶኛል ፤ መዋረድ መብከቱ ።

አሻሮ ናት ምሴ ፤ እንኩሮም አልጠላ
አንድነት እርሜ ነው ፤ ልስራ ለግንጠላ
ጫን ያለው ሲመጣም ፤ ይኮናል አተላ
ምሴን አትንኩብኝ ፤ ኋላ እንዳንጣላ ።

ታዛቢው ... August 27/2011